# የምጽአቱ የምስራች

ቅጽ 78 ቁጥር 5(929) ÷11 (935) ‹‹ እኔ ቅዱስ ነኝ እና ቅዱሳን ሁኑ›› ‹‹ በቶሎ እመጣለሁ›› ራዕይ 22÷20

## መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ዳግም ምጽአትን በቅድስና መጠበቅ

"ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና" ዕብራውያን 12÷14

በኮሚኒስቶች ዘመን የሮማንያ ሕዝብ ለ20 ዓመታት በአምባገነኑ ቻውቼስኩ ስር ሲማቅቅ ኖሯል። በአገራችን ኢትዮጵያም በተከታታዮቹ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መንግስታት፤ በደርግና ወያኔ ሕዝባችን የደረሰበት መከራ እጅግ የከፋ ነበረ።

በማርክሲስት ሀገሮች ወንጌልን መስበክ በአዋጅ በህግ የተከለከለ ነበር። በድብቅ ቤተክርስትያናቸው የተወረሰባቸው ምዕመናን ለፀሎት ሲሰበሰቡ ተይዘው ይታሰሩና ይገረፉ እንደነበር እራሴ ይህንን የምጽፈው ያየሁት ሕያው ምስክር ነኝ።

ማርክሲስት መሪዎች ከምዕራቢያውያን ከሚደርስባቸው ጫናና ማዕቀብ ህጋቸውን ለዘብ ሲያደርጉ የመስበክ ፍቃድ በመጠኑ ይገኝ ነበር። በዚህ ሁኔታ የታገደውን የመስበክ መብት ድጋሚ ያገኘው የሮማንያ ፓስተር ይህንን እድል ለምእመናኑ ብቻ ሳይሆን ለመላው የሮማንያ ሕዝብ ወንጌል ይደርስ ዘንድ ለመንፈሳዊ መነቃቃት አብዝቶ መጸለይ ጀመረ።

በውጪ ካሉት ከማያምኑት ባልተለየ በክርስትያኖች ህብረት ውስጥ ያሉትን በሙሉ ሐሴት በማድረግ የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ ይሆኑ ዘንድ ደከማ አማኞች ሆነው ከመንግስት ካዝና የሚሰርቁ ተገቢውን የመንግስት ቀ ግር የማይከፍሉትን ጭምር የሚወቅስ ብርቱ መልዕክት ማስተላለፉን ቀጠለ።

ሌላው በወቅቱ በሩማንያ የነበረው የአልኮል መጠጥ ሱስ በክርስትያኖችም ዘንድ በጣም የተስፋፋ ስለነበር መስከር ሀጥያት መሆኑን አበክሮ ማስተማር ስራው ሆነ።

በዚህ ሁኔታ የሮማንያ ሕዝብ በአስደናቂ የቅድስና ልምምድ ውስጥ ገባ። በአልኮል መጠጥ በመስከር ሌብነት፤ዝሙት፤ስርቆት ይፈጽሙ የነበሩ ሰዎች ከነዚህ ክፉ ድርጊቶች ተቆጥበው በሀገሪቱ የመንፈሳዊ መነቃቃቱና የቅድስና ኑሮው በጣም ተስፋፋ።

በቀጠለው እንቅስቃሴ መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳቸው 150 ሰዎች ኦራዳ በተባለች ከተማ በ1966 ቅዱስ ጥምቀትን ፈፀሙ። በዚያን የማርክሲዝም ዘመን በክርስትና በይፋ ማመን መመስከር የህይወት ዋጋ የሚያስከፍል መስዋእትነት መቀበልን የሚጠይቅ ውሳኔ ነበር።

የመንፈሳዊ መነቃቃቱና ቅድስናው በአንድ ከተማ ብቻ ሳይወሰን በመላ ሩማንያ የተቀጣጠለና ለብዙዎች የደረሰ ሆነ። በመንፈሳዊ መነቃቃትና ቅድስና የተሞሉት ሰዎች ያለምንም ፍርሀት በየስፍራው ስለክርስትና መመስከር ቀጠሉ። በኦራዳ ከተማ የነበረች ቤተክርስትያን በፓስተሩ አማካኝነት ከክፉ ልምምዶች በመራቅ በመንፈሳዊ መነቃቃትና በቅድስና በመሞላት በሩማንያ ከነበሩ አብያተ ክርስትያናት የተለየች በመሆን በመንፈስ ቅዱስ ቅድስና የተለማመደች ነበር። የአማኞች ድክመት የሚከሰተው ሰዎች የክርስቶስ ምሳሌ መሆን ሲያቆሙና ዓለምን እንዲመስሉ ምክንያት ሲሆኑ ነው።

የክርስትና ልዩ ባህርይና ሀያልነት ዓለምን መምሰል ወይም ከአለማዊያን ጋር መመሳሰል ሳይሆን በቅድስና በመለየት ከዓለማዊነት በመራቅ በዓለም ውስጥ በጨለማ ብርሀን መሆን ነው።

በዚያን የማርክሲስቶች ጨካኝ የኮምኒዝም አገዛዝ ዘመን ጌታን በማመኑ በመመስከሩ በመስበኩ በኮምኒስት ባለስልጣኖች ተይዞ ብዙ ግርፋት እስራትና መከራ የተቀበለው ‹‹ ለክርስቶስ ተሰቃየሁ›› የሚለው መጽሐፍ ደራሲ ቄስ ሪቻርድ ውምብራንድ አንዱ የክርስቶስ ህያው ምስክር ነው።

ዛሬ በዓለም ዙሪያ በክርስትና እምነታቸው የሚሰቃዩትን የሚደግፍ መንፈሳዊ ማህበር በተከታዮቹና በልጆቹ ተዋቅሮ ይህን የምፅፈው ራሴ በአንዱ ሥፍራ ኦካላሆማ ዌስሌ ቤተክርስቲያን የልጁን የሚካኤል ውምብራንድ መልእክት ሰምቻለሁ።

በዘመናችን የመንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች መኖር የመነቃቃት መኖርን አያረጋግጥም። ልዩ ልዩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ኮንፈረንሶች ኮንሰርቶች ውይይቶች (ምክክሮች) በመገናኛ ብዙሃን ኢንተርኔት በሚድያ በብዛት ቢኖሩም ተፈላጊው ለውጥ አልተገኘም። ለምን? ብዙ ሰዎች ይሰበካሉ ያምናሉ ነገር ግን ትክክለኛ የህይወት ለውጥ የሚያገኙት ግን ጥቂቶች ናቸው።

የእግዚአብሔር ጉብኝትና በረከት ወይም መንፈሳዊ መነቃቃትና ተሃድሶ የማይገኘው የተለወጠ የአማኞች ህይወት በሙላት የማይታየው በሌላ  በምንም ምክንያት ሳይሆን ባለመታዘዝ ሀጥያት ነው። ይህም በግልጽ ንግግር በቅድስና መጉደል ብቻ ነው።

‹‹በአሕዛብ መካከል ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱሱ ስሜ ነው እንጂ ስለ እናንተ የምሰራ አደለሁም›› (ሕዝ. 36÷22) የእግዚአብሔር ስራ በግልፅ በህይወታችን፤ በቤተሰባችን፤ በከተማችንና በሀገራችን አልፎ ተርፎ በመላው ዓለም ይሰራ ዘንድ በቅድስና መጠበቅ ያስፈልጋል። የቅድስና ጉዳይ በዋዛ በቀልድ የሚታይ አደለም።

ሰዎች ከራሳቸው ከቤተሳበቸው ወይም ከሀገራቸው ቅድስና ይልቅ ለሌሎች ነገር በጣም ግድ እያላቸው የእግዚአብሔርን ጉብኝት መጠበቅ የእግዚአብሔርን ሰላም መመኘት ዘበት ነው።

የአማኞች ህብረት በትዳር፤በገንዘብ በስራ በትምህርት በተለይ በዚህ ዘመን በፖለቲካ ቅዱስነቱ ሳይጠበቅ ሰላም፣በረከት፣አንድነት ይገኛሉ ብሎ መጠበቅ እንደ ምሳሌያችን ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ ነው።

ክርስቲያኖች እራሳቸውን በቂም በዘረኝነት በትእቢት፤በንቀት፤በጥላቻ ተሞልተን ሌሎች በፍቅርና በሰላም በአንድነት እየበለጡን የምንገኝበት ዘመን ላይ ነን።

በቅርቡ በሀገራችን የታዩት አሰቃቂ ወንጀሎች መገዳደሎች  የተፈፀሙባቸው ሥፍራዎች መሰባሰቢያ ጭምር የፍቅር የወንጌል መስበኪያ አዳራሾች መሆናቸው እጅግ በጣም  የሚያሳፍር ሆኗል።

በማርክሲስቱ ኮሚኒስቶች ዘመን በክርስትና ለመገረፉ፤ለመታሰር፤ለመገደል ዝግጁ የነበረው ትውልድ ዛሬ ለብሔር ለዘር ለፖለቲካ በማለት የአባቱን የክርስቶስን ልጅ የሚጠላበት አልፎ አልፎም የሚያርድበት ጊዜ ላይ መሆናችን በጣም ያሳዝናል።
የእግዚአብሔር በረከት ለግል ልምምዳችን ህይወታችን፤ለቤተሰባችን፤ለከተማችን፤ለሀገራችን እንዳይፈስ እንቅፋት የሆነውን መሰናክል ኃጢያታችን ይቅር ያለማለታችን ፍቅር የራቀው ህይወታችን

ስለሆነ ዛሬውንኑ ለጌታ የሚሳነው የለምና በንስኃ እንስተካከል። (ኢሳ 55÷7)

**ወደ ሚቀድሰው ጌታ ቅረቡ**

**በሪች ካርማይክል - አሳታሚ**

የዚህ እትም የምጽአቱ የምሥራች አብይ ጉዳይ ቅድስና ይሆናል።
ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ በቅዱስ መጽሐፍ ጌታ ማንም ያለቅድስና እርሱን ማየት እንደማይችል ስለተናገረ ነው። (ዕብ. 12÷14)

ጌታ አማኝ ልጆቹን የመረጠን ለቅድስና ነው። (ኤፌ.1÷4) (1 ጴጥ 1÷16)

የእግዚአብሔር ፍቃድ እንድንቀደስ ነው በቅድስናም የጌታ ፍርሃት ይኖረናል።

(1 ተሰሎንቄ 4÷7) 2 (ቆሮ 7÷1)

ለጌታ ክብር መስጠት የምንችለው በቅድስና ሲሆን በእርሱ ክብር የምንሞላውም በቅድስና ይሆናል። (2 ተሰ 1÷10፣ 2÷13)

የእግዚአብሔርን ቅድስና የምንቃወም ከሆነ የምንቃወመው እራሱን ጌታ ነው።
( 1ተሰሎንቄ 4÷8)

በዚህ እትም የሚገኙትን ልዩ ልዩ ርዕሶችና ዝርዝሮች በምታነቡበት ወቅት ሁለት ከቅድስና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ትረዳላችሁ እነርሱም ፡- ቅድስና የእግዚአብሔር እቅድ መሆኑና እኛም በእግዚአብሔር ብቻ መቀደስ እንደምንችል ነው። (ዕብራውያን 9÷13፣ ዮሐ 17÷17)

እውነት የሆነው የጌታ ቃል ከእግዚአብሔር የጸጋ ዓላማ የተነሳ እርሱ እግዚአብሔር ሊቀርበን እንደሚችል ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጣል። (2 ጢሞ 1÷9፣ ዕብ 2÷11) ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ የእኛ የክርስቲያኖች የጽድቅ የመቀደስና የመቤገርት ምክንያት ነው። (ዕብራውያን 2÷11፣13÷12)

ጽድቅ፤መቤገርትና መቀደስ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነሳ ይሆንልናል። ሁለተኛው አብይ ጉዳይ ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ የተወሰነ ነው። በውጪ ህይወታችን በመትጋት ከጌታ ጋር ያለን የግል ግንኙነት ግብዝነትና የማስመሰል የሀሰት ስራ ካለበት ቅድስና የለም።

ቅድስና በግላችን ከጌታ ጋር ባለን እውነተኛ ግንኙነት የሚያድግና ምሉእ መሆን የሚችል ጉዳይ ነው።

ስለዚህ በዚህ እትም ያሉት የምጽአቱ የምሥራች የመልክትና የትምህርት ዓላማዎች ዘወትር በክብርና በሥልጣን ፀንቶ ወደሚኖረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንድንቀርብ የሚያተጋን የሚያሳስበንና የሚያዘጋጀን ይሆናል።

ተስፋችን አማኞች በቅዱስ ቃሉና ይህን በመሰሉ ቃሉን መሰረት ባደረገ መልዕክቶች ከጌታ ጋር ንቁ ግንኙነት ያለንና ከክፉ ዓለምና ከክፉ ስራዎች የተለየን መሆን ይጠብቅብናል። (ሕዝ. 15÷11፣ዕብ 7÷26)

**ቅድስናን ሙሉ (ምሉእ) ስለማድረግ**

"እንግዲህ ወዳጆች ሆይ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሀት ቅድስና ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንፃ።" (2 ቆሮ 7÷1)

ቅድስና ምን እንደሆነ እናውቃለን? ቅድስና እግዚአብሔር የሚያጎናፅፈው ነው። መለየት መንፃት መሰየም ቅድስና አይደለም የቅድስና መዳረሻ መንገዶች እንጂ ቤተ መቅደሱ ቅዱስ የሆነው ጌታ ስለገባበት ነው። ለጌታ የሚቀርብ ሁሉ የተቀደሰ አይደለም ጌታ የተቀበለው ብቻ የተቀደሰ ነው።

እግዚአብሔር የተቀበለውን ይባርካል ይቀድሳል ወደራሱ ህብረትም ያስገባል፡፡

ጌታ ራሱ እኔ የምቀድስህ አምላክ ነኝ ብሎናል፡፡ የቅድስና መሰረቱ ጌታ ራሱ "ተቀደሱ" ብሎ በቅዱስ ቃሉ ባዘዘው መሰረት የሚከናወን ነው፡፡(ዘሌ. 20÷7)

እኛ ክርስትያኖችም የምንቀደሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስትያኖችን ቅዱስ መፅሀፉ 'ቅዱሳን' የሚላቸውን በዚህ ምድር ስንጠየቅ ስንጠራ 'ቅዱሳን' የሚለውን የጋራ መጠሪያችን የተገባ ጉዳይ ነው፡፡ ጌታ ከእኛ ጋር እንደሚኖር በቃሉ አረጋግጦናል፡፡

እምነት ምስጢራዊ ተፅእኖ በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትል የአማኞች ዋና የመንፈስ ፍሬ ነው፡፡ ይህን የጌታን ስጦታ የሚያቀረፍዱ ልንፀልይላቸው ይባስ ጉዳት እንዳያመጡ ልንለያቸው ይገባል፡፡

በየእለቱ ነፍሳችንን፤ስጋችንንና አእምሮአችንን የሚጎዱ ነገሮች ከእኛ ይርቁ ዘንድ በጥሞና ልንፈትሽ ይገባል፡፡

ይህንን የማዳን ፀጋ ከጌታ እንዳገኘን እኛም በተራችን ይህን የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ የሆነውን ለሌሎች ይደርስ ዘንድ ያሉትን መንገዶች ሁሉ እንጠቀም፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በዝማሬ ሀሴትን ማድረግና የመሳሰሉትን ሁሉ በጎ ምግባሮች የምናገኘው ሁሉም የሰው ዘር ከፈጠረበት ክርስቶስ መነሻነት ይሆናል፡፡

ከእነዚህ ሁሉ አገልግሎቶችና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች መሀል ዋነኛው ሊጠቀስ (ሊፖስት) የሚገባው ጉዳይ እምነት ሲሆን እምነታችንንም በየጊዜው በምንሰማው መልዕክትና ምስል እንቅስቃሴ ከወቅቱ ጋር ሊጠኑና ሊሻሻሉ ይገባል፡፡ በየእለቱ የምናደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከማለዳ ጀምሮ በክርስቶስ ደም ይቀደሱ ዘንድ በጸሎት አሳልፈን መስጠት ይገባል፡፡

የክርስትያኖች ትልቁ ለውጥና ዕድገት በውጭ የሚታይ ሳይሆን ድብቁ የጸሎት ህይወትና የሰይጣን ተቃውሞ በሚገባ የሚፈፅም አገልግሎት ያስከትልናል፡፡ በማርቲን ሉተር አባባል በቅድስና ህይወት ለመጠበቅ ጌታ ትናንት እንደጠራን ዛሬ እንደመገበንና እንዳስተማረን ነገ ባላመኑት ላይ በይፋ እንደሚፈርድ አምነን እንትጋ፡፡

## ከጌታ ጸጋ በኃጢያት አንጉደል

የእግዚአብሔር አገልጋዮች የተሰጠንን ሀላፊነት በሚገባ ለመወጣት እርምጃችን ንግግራችን ጽሁፋችን የመሰሉ ስራዎችን በሙሉ በጌታ መንፈስ እንፈፅመው፡፡

በጌታ ሥራ አገልግሎት ከተሰማራን በኃላ የምናደርጋቸው ንግግሮችና የመልዕክት ልውውጦች በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሊካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎችን ወደ ጌታ መንግስት ለመጨመር የምናደርገው ነገር ሁሉ በተገቢ ዓላማና ድርጊት ይፈፀም፡፡

በልዩ ልዩ ባህሎችና መንግስታዊ ህጎች ሰራተኞች የኃላፊነቱን ደረጃና ብርታት በሚገባ እንደሚጠብቁት የክርስትና አገልጋዮች መመሪያቸውን መጽሐፍ ቅዱስን የተከተለ ገለጻ አገልግሎትና ግንዛቤ ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡

አማኞች በወንጌል በመሪያቸውና በአምላካቸው ጌታችንና መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር የሚታመኑና የሚፎክሩበት ሊሆን ይገባል፡፡ ሆኖም ግን መልካሙ ኃያማኖታችን ባህላችን ሲበላሽ ተመልክተን ማለፍ የለብንም፡፡

በጌታ ዘንድ አንዳች የሰው ዘር አይነት ልዩነት እንደሌለው ሁሉ እኛ አማኞችም በያለንበት ሰፈር፣ከተማና ክልል ሁሉ ሰዎችን የሚደግፍ የሚያሳድግ የሚገነባ መልካም መልእክት ብናቀርብ ውለታው የሰዎች ሳይሆን የጌታ ሲሆን ክፉ ሥራችን ከሆነ ደግሞ የክፋቱ ውጤት ይከተለናል፡፡

**የእግዚአብሔር የቅድስና ዓላማዎች**

"አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሰራዊት ጌታ እግዚያብሔር እያሉ ይጮሁ ነበር፡፡" (ኢሳ 6÷3)

እግዚአብሔር ከመሰረቱ ቅዱስ ነው፡፡ የከበቡት መላእክት ኪሩቤልና ሱራፌል በሁሉም የሚታይ ሀይል ያለው ብለው የሚጮሁ ሳይሆን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ለእግዚአብሔር የሚያውጁ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ለዘላለም የሚጠብቅ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን የትም የማይገኘውን ሰላምና ደስታ እናገኛለን፡፡

በእግዚአብሔር ፊት መቆም እጅግ የሚያስፈራና የሚያንቀጠቅጥ መሆኑን ነቢዩ ኢሳያስ ወደ ጌታ ዙፋን በቀረበ ወቅት የተናገረውን ማገናዘብ ይቻላል (ኢሳ 6÷5)

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰውን አይፈራም በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት የሚንበረከክ ሰው በምንም ነገር ፊት መቆም ይችላል፡፡

በየእለቱ ይህን ክብር ምስጋና ፍርሃት የሚገባውን ጌታ በጸሎት መገናኘት ለብዙ ብርታት ፅናት ደስታ ሀሴት ፍቅር እየሰጠን ለዚህ ዘመን መድረሳችንን ከተጻፋልን አያሌ መጽሐፍት እናነባለን፡፡

የእግዚአብሔር ቅድስና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእኛም ቅድስና ዋና ግብ ወይም ራዕይ ነው፡፡

**በኃጥያት በጨቀየ ዓለም በንፅህና ስለመኖር**

በትክክል ከእግዚአብሔር ዳግም ከመንፈስና ከውሀ በቅዱስ ጥምቀት የተወለድን ከሆነ እግዚአብሔርን በየቀኑ የመምሰል የመፈለግ የማክበር ፍላጎት ይኖረናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የመምሰል ፍላጎት ከሃዋሪያው ጳውሎስ ጀምሮ በቅዱሳኑ አማኞች ሁሉ ዘንድ ይኖራል፡፡ ለዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች እኛ እንዴት ቅዱሳን ለመሆን ተሰራን? እግዚአብሔር ቅዱሳን አድርጎ የሰራን መቼ ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ሰው ኃጢያት በሰራ ግዜ የሸፈነው የእግዚአብሔር ጸጋ ይነሳና እራቁት መሆኑን ይረዳና በሀፍረት ይሞላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሄዋን የደረሰባቸው ይህ ነው፡፡ (ዘፍ 3÷10)

ሆኖም ግን አግዚአብሔር በኃጥያት የወደቀውን የሰው ዘር ከሴት በተወለደው ልጁ በገባው የተስፋ ቃል መሰረት አዳነው (ዘፍ 3÷15፣ገላ 4÷4)

በኃጥያት የወደቀው የሰው ዘር የተቀደሰውና ከፈጣሪው አምላክ ጋር የታረቀው በደም በተደረገ ክቡር ታላቅ ቃልኪዳን ነው፡፡

ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢያት በመስቀል ሞትና በትንሳኤው ያመኑት መዳን ብቻ ሳይሆን በብርሀን በመመላለስ በቅድስና ህይወት ለሌሎችም ትምህርት ሰጭ አገልግሎት ዘላለማዊ እድል ነው፡፡

'የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢያት ሁሉ ያነጻል፡፡' (1ኛ ዮሐ 1÷7)

የሰው ዘር ከወደቀበት ኃጢያት አዘቅት በመውጣት የቅድስና ህይወት ሊኖር እንደሚ ችል በነብያት በኩል የመሲሁ የክርስቶስን መከራና ሞት የማዳን ሰላማዊ ስራ ተንብየዋል፡፡

'በማስጨነቅ በፍርድ ተወገደ ስለ ሕዝቤ ኃጢያት ተመትቶ ከሕያዋያን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ።' (ኢሳ 53÷8)

ሰዎች ይህንን በእግዚያብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋትነት ያገኘውን ነፃነትና ቅድስና ክርስቶስን በማመንና በመከተል ይቀዳጃሉ።

‹‹እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ›› ማቴ 16÷24)

ሀዋርያው ጳውሎስ ይህንን በመልእክቱ ላይ አስረግጦ በመናገር 'ኃጢያት መስራት እንቀጥልን?' ብሎ በመጠየቅ 'አይሆንም አይደረግም' ብሎ መልሷል 'ኃጢያትን እንስራን? አይደለም' (ሮሜ 6÷15)

አማኞች ከኃጢያት ጋር በየቀኑ በመፋለም በክርስቶስ ደም ኃይል ነፅተው ተቆጥበው ይኖራሉ። (ሐዋ 1÷4፣ኤፌ 5÷25፣1 ጴጥ 1÷22)

**ቅድስና ክርስቶስን በመምሰል ይገኛል**

የቅድስና ህይወት ክርስቶስን በመምሰል ማደግን ያካትታል። መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን እንድንመስል ሲለውጠን ምንኛ ደስ ይላል።

'ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና።' (ማቴ 11:29)

የክርስቶስ ተከታዮችም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቃቸው ልጁን ኢየሱስ ይመስሉ ዘንድ የጠራቸው ናቸው። ክርስቲያኖች እውነትን በፍቅር በመግለፅ ወደ ክርስቶስ ሙላት ይደርሳሉ።

የእግዚአብሔር ልጆች እድገት ሥርአት እንደሚከተለው ነው። ቅድስና ክርስቶስን የመምሰል ሄደት ሲሆን እውነትን አማኞች በመሰሉ ቁጥር ቅድስናቸው እያደገ ይመጣል። በተቃራኒው ክርስቶስን ከመምሰል እየቀነሱ ሲመጡ የበለጠ ክፋት፣ አመፅና ነውር የሞላባቸው ይሆናሉ። ስንቶቻችን የክርስቶስ ነን እያልን ከክርስቶስ ባህሪያት የራቀ የሚፃረር ድርጊትና ህይወት ያለን ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል ዘወትር በመፈተሽ ብንኖር ክርስቶስን የመምሰል ምስጢር ይገባናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ በሚገባ መመላለስና ጌታን ማስደሰት ቅድስና ነው።

ጌታችን ኢየሱስ የተናገረው መሰረታዊ ቃል ያለ እሱ ምንም ማድረግ ያለመቻላችን ነው። (ዮሀ 15÷5) በራስ መተማመን በራስ መኩራራት የራስ ብቃት የምንለው ሁሉ ሊሰቀል የሚገባው ነው። እኔነት የክርስትና ሆነ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ነው።

በጌታ ዘንድ ግን ብርቱ ደካማ ደካማው ብርቱ ይሆናል ይህም የእግዚአብሔርን ማዳንና ብርታት በሰዎች ድካም እንደሚገለጽ ቅዱስ ቃሉም ኑሮም ይመሰክራሉ።(2 ቆሮ 12÷10፣ፊል 4÷13)

የእግዚአብሔር እውነት የቅድስና ትልቁ መሳሪያ ነው።

'በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው።' (ዮሀ 17÷17)

መንፈስ ቅዱስ ዘወትር የሚቀድሰው እግዚአብሔር ቃሉን በሚገባ እያጠኑ ራሳቸውን ለቃሉ ለሚያስገዙ ነው።

በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተገኘው ሥርዓት ቅድስና የሚያጎናጽፈው በእግዚአብሔር ቃል በተፃፈው መሰረት በደም የሚገኘውን መቤዡት በክርስቶስ የመስቀል ላይ መከራና ደሙን ማፍሰስ የተከናወነ በመሆኑ ነው። (1ዮሐንስ 1÷7 ቲቶ 2÷14)

## ለቅድስና ሕይወት የቀረበ ጥሪ

‹‹ምን ብልጫ ታደርጋለችሁ?››

(ማቴ 5÷47)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም ሕይወት ሰጭው ለተከታዮቹ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ክርስቶስን ያመኑት ከሌሎቹ በክርስቶስ ከማያምኑ በተሻለና ጌታን የሚያስከብር ስራ ለመፈፀማቸው መጠየቁ ነው፡፡

ይህን ጥያቄ ጌታ ለተከታዮቹ ያቀረበው ክርስቶስን አምነናል ብለው ተመልሰው በኃጢያት የተያዙትን በውጭ ሁኔታ ብቻ እምነታቸውን ማሳየት ለሚፈልጉ የቀረበ ብርቱ ጥያቄ ነው፡፡

ክርስቲያኖች በክርስቶስ እናምናለን የሚሉ ከሆነ የክርስቶስ ልብ አሰራር ምስክርነትና መሰጠት ሊኖርባቸው ይገባል፡፡

ማናችንም በክርስቶስ በማመን አዲስ ልደት አግኝቻለሁ አምኛለሁ ስንል በውስጣችን ያለ የድሮ እርሾ የዓለምና የሰይጣን እርሾ እንዲወገድ በብርቱ ፀሎትና ፆም መትጋት አለብን፡፡ ማናቸውም ልምምድና ግንኙነት በክርስቶስ መከራና ሞት ያገኘነውን ህይወት የሚገፋ የማይቀበል የሚጻረር ለመሆኑ በመፈተሽ ከክፉ መራቅ ይገባናል፡፡

እግዚአብሔርን በሙሉ መታመን እንደቃሉ እንደሚባርከን የተስፋ ሕይወት እንዲሰጠን ልንማጸነው ያሻል፡፡

የክርስቶስ ተከታዮች ከሌላው ተከታዮች በብዙ ብቃት እንደሚኖሩ ከተባፈው አማኞች ተረድተው የበለጠ በበጎ ሥራቸው እንዲቀጥሉ ማትጋት ያስፈልጋል፡፡

ጌታ ይህንን የብልጫ ጥያቄ ለተከታዮቹ ያቀረበው ተከታዮቹ ለሰዎች ሊያደርጉ የሚገባውን በጎ ነገር ከሌሎች ጋር በማነፃፀር ተከታዮቹ በደግነትና በበጎ ስራ የላቁ የበለጡ እንዲሆኑ ለማሳሰብ ነው፡፡ ይህን የበለጠ በጎ ስራ አንዳንድ ክርስትያኖች ሲያደርጉት የቀሩት ግን ያለማድረጋቸው የሚያሳዝን ሲሆን በተቃራኒው በክፋትና የሌሎችን መብትና ማንነት የሚንቁ የሚያጣጥሉ በጣም ያሳፍራሉ፡፡

በጌታ ዘንድ በኃይሉ ችሎት የበረቱ እንዲሆኑ ክርስትያኖች ጥሪ የሚቀርብላቸው ሌሎችን በመጉዳት በማማረር ሳይሆን እንደ እምነቱ ጀማሪ ክርስቶስ የራስን ህይወት እስከመስጠት በማገልገል ነው፡፡

እግዚአብሔር በእውነት የሰጠን ድል በውስጣችን ያለውን ኃጢያት ክፋት ጠማማነት ከማስወገድ ይጀምራል (1ቆሮ15÷57) የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነው ክርስትያን በደግነት በበጎነት በሰላማዊነት ሕዝቤ ብሎ የጠራውን ጌታ የማያሳፍር መልካም ሕዝብ ሊሆን ተጠርቷል፡፡ (ማቴ 5÷48)

## ቅድስና የመንፈሳዊ ተሀድሶ ፍሬ ነው

ነቢዩ ኢሳያስ በመጀመሪያዎቹ አምስት ምእራፎች ‹‹ወዮ ለእነርሱ›› ያለውን መልእክት በምዕራፍ ስድስት ላይ‹‹ወዮ ለእኔ›› ብሎ ቀይሮታል፡፡ በዚህ ጉዳይ መለወጡ መቀደሱ መባረኩ የግል ጉዳይ ይሆናል፡፡

ቅዱስን እግዚአብሔር በሚያስደንቅ ሁኔታ በሱራፌል ኪሩቤል ተከብቦ በተገለጠበት ወቅት ነቢዩ ኢሳያስ ማንነቱ እጅግ ስለተሰማው ጉዳዩን ወደ ግል ህይወቱ በማምጣት ‹‹ወዮ ለእኔ በማለት በጌታ ፊት ልባዊ ኑዛዜ አድርጓል፡፡

በመንፈሳዊ መታደስ መነቃቃት ጅማሬው ሰዎችን ወደንስኃ በመጥራት ሳይሆን እራስን በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ በመፈተሽ አመድ ለብሶ

ዱቄት ነስንሶ ደረትን በመድቃት በእንባ ጸሎት ወደ ጌታ ከመመለስ ይጀምራል፡፡
ዛሬ በብርቱ የሚያስፈልገን መንፈሳዊ ጉዳይ በዚህ ሁኔታ ጌታ በትክክል ከተገለጠልን ራሳችንን በእግሩ ስር በመጣል የእሱን ጉብኝት ለቤተሰባችን፤ለሀገራችን ለመላው ዓለም መፈለግና ማድረግ ነው፡፡

‹‹ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች››

ነብዩ ኢሳያስ ወደ እግዚአብሔር በንጹህ ልብ በቀረበ ግዜ ራሱን በትህትና ሲያዋርድ የእግዚአብሔርን ክብር አየ፡፡ ደቀመዛሙርቱ አየ በዚህ ሁኔታ ራሳቸውን ሲያዋርዱ አዩ፡፡ (ሐዋ 4÷31)

እንደ ነብዩ ኢሳያስ እንደሐዋርያቱ ዘመን ‹‹ወዩ ለእኔ›› ብለን በእውነተኛ ንስኃ በእግዚአብሔር ፊት ሳንቀርብ አንዳች የእግዚአብሔር ጉብኘት ሊገኝ አይቻልም፡፡ ኢሳያስ "ከንፈሮቼ የረከሱብኝ" በማለት ሁሉንም የነበረውንም ማህበረሰብ ገለፀ እንጂ አንደዘመናችን ግብዝነት የድፍረት ኃጢያት ከዓለም የባሰ ክፋት መገዳደሉ ዘረኝነቱ በሚያምኑት መካከል ሳይቀር እየታየ በሽንገላ "ከንፈር የተባረከ ሕዝብ የተቀባ ህዝብ" በማለት ሊደረግ የሚገባውን ብርቱ ንስኃ አላደናቀፈም አልገታም፡፡

በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ እንደምናየውም ሆነ በመንፈሳዊ ተሀድሶና መነቃቃት በተከሰተባቸው ሁኔታዎች በኃጢያት ጨለማ በተዋጡ ማህበረሰቦች መካከል ኃጢያቱ የሚያሳስባቸው የእግዚአብሔር ሰዎች በብርቱ የንስኃ የእንባ ፀሎት በቅዱስ ቃሉ ሙላት ያስጀመሩት እግዚአብሔር መንፈስ ስራ ነው፡፡

‹‹አቤቱ ትመለሳለህ ታድነንማለህ ሕዝብም በአንተ ደስ ይላቸዋል፡፡ (መዝ 84÷6)

ከፍ ያለውና የተቀደሰው ጥሪያችን

የክርስቶስ ሐዋርያ ቅደስ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ቤተሰቦች ማህበረ ምእመናኑ መልእክቱን በሚጽፍበት ወቅት አማኞችን "ቅዱሳን" ብሎ በመጥራት ይጀምራል፡፡

‹‹በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ (ሮሜ 1÷7)

‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት›› (1ኛ ቆሮ 1÷2)

‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ››

(ፊሊ 1÷1)

(በቆላስይስ ለሚኖሩ ቅዱሳንና በክርስቶስ ለታመኑ ወንድሞች (ቆላስይስ 1÷2)

አማኞች ሁሉ ሐዋርያው ጳውሎስ ቅዱሳን በማለት ይጠራቸው ነበር፡፡ ይህ ማለት ግን እነዚህ ወገኖች በሙሉ እኛ የምንረዳው የቅድስና ባህሪያት ዘወትር ይገኙባቸዋል ማለቱ አይደለም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ አልፎ አልፎ በሚያጋጥሙት የአማኞች ኃጥያትና በደል እጅግ ማዘኑን የሚያመላክቱ ቃላቶቹን በመልክቶቹ ውስጥ እናገኛለን፡፡ ይህም ሆኖ ግን ሐዋርያው ቅዱሳን ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

ይህ መጠሪያ ጌታ ለአማኞቹ የሰጠው ፍቅር መጠሪያ እንጂ የጳውሎስ ጥሪ ወይም ዘይቤ ሆኖ አይደለም፡፡

ቅዱሳን ማለት የተለዩ ሆኖ በበጉ ደም የነፁ ማለት እንጂ ኃጢያት የማይገኝባቸው ማለት አይደለም፡፡

የራሱን ትግል እያነፃፀረ ሐዋርያው ጳውሎስ የአማኞችን የየቀኑ ፈተናና ድካም በመረዳት በቅድስና በትጋት ይመላለሱ ዘንድ በመልክቶቹ ያሳስባቸው ነበር፡፡

‹‹ በኃላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ›› (ፊሊ. 3÷14)

ወጣቱ ጢሞቲዎስን በቅዱስ አጠራር የጠራህ ማለቱ የቅድስና ጥሪና መለያ ከጌታ መሆኑን ያረጋግጣል (2 ጢሞ 1÷9)

የተሰሎንቄ ወገኞችም ለእግዚአብሔር የክብር መንግስት እንደተጠሩ ያሳስባቸዋል፡፡

‹‹ወደ መንግስቱም ወደ ክብሩ ለጠራችሁ እግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጽናናን›› (1ተሰሎንቄ 2÷11)

በዕብራውያን መልእክት ላይም የሰማያዊ ጥሪ የሚለው የቅድስና ጥሪ ከእግዚአብሔር መሆኑን ያሳያል፡፡ (ዕብ 3÷11)

ሐዋርያው ጴጥሮስም እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ነኝ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ያለበትን መልክት ጽፏል፡፡ (1ጴጥ 1÷15)

'መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታፀኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፡፡' (2 ጴጥ 1÷10)

'እርሱን እንድንመስል እናውቃለን'

(1 ዮሐ 3÷2)

የተወደዳችሁ አማኞች ጌታ ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ድንቅ ብርሀኑ የጠራን ልዩ ቅዱስ ጥሪ ነውና እናክብረው፡፡ (ጴጥ 2÷9)

**ቅዱስ መንፈሱ በብዙ ያስፈልገናል**

ዛሬ ቤተክርስትያንን እጅግ የሚያስፈልጋት ምንም ሳይሆን በቅዱስ መንፈስ የተሞሉ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ናቸው፡፡

ቤተክርስትያን የቀደመ ፍቅሯን ትታለች (ራእይ 2÷4) ስለዚህም ብርቱ የነበረው ገሃነም ደጆች የማይቋቋሙት ኃይሏን አጥታለች፡፡ (ማቴ 16÷18)

በየስፍራው የአባላት ለውጥና ቁጥር በየአብያት ክርስቲያንቱ በመቀነስ ላይ ነው፡፡ 'በእየእለቱ የሚድኑትን በህብረት ላይ ይጨምር ነበር' የሚለው እየቀረ ነው፡፡ (ሐዋ 2÷47)

ዘመናችን ቤተክርስትያን በድሮ ዘመን ያልነበሩ አያሌ ስልጣኔዎች ጥቅሞችና በተቃራኒው ተግዳሮቶች እየገጠሟት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የእግዚአብሔር ክብር ከቤተክርስትያን እየለቀቀ ነው፡፡ ይህ ኢካቦድ ጥንት ነበረ ተደገመ፡፡ (1ኛ ሳሙ 4÷21) በቁሳቁስ የተሞላ ዘመናችን ፈሪኃ እግዚአብሔርና አምላካዊ አስተሳሰብ እየራቀው ይገኛል፡፡ ይህን የሚረዱ መንፈሳዊያን ብቻ ስለሆኑ ለመፍትሄውም ጌታ ያስቀመጣቸው እነርሱን በመሆኑ ይህን የምታነቡ ሁሉ ባላችሁበት ስፍራ ለመታደስ ለመነቃቃት ህዝቡን ከሚመጣው ቁጣ ለማትረፍ በጸለትና በቃሉ ተግታችሁ ተሰማሩ ምንም ቸልታ አይያዛችሁ፡፡

የዛሬው ዘመን ቤተክርስትያን ለትውልድ ያለባት ኃላፊነት ካለፈው ዘመን እጅግ የበለጠ ነው፡፡ የሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት ሲጨምር ሚሊዮኖች በእግዚአብሔር ቤት ላይ በይፋ ሲነሱ ወንጌል የሰበከ ሰው በታላቂቱ አሜሪካ ጭንቅላቱን ተመትቶ ደም ሲፈስው ሌሎቹ ችላ ሲሉ ማየቱ ምን ያህል መንፈሳዊነት ከህዝቡ መጥፋቱን ያመላክታል፡፡

ዛሬ ክርስቶስን ያላወቁ ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች ደም በቤተክርስትያን እጅ ላይ ይገኛል፡፡ (ሕዝ 3÷18)

ቤተክርስትያን የዛሬውን ዘመን ያህል ለወንጌል ሥራ ምቹ ሁኔታ ያገኘችበት ጊዜ የለም፡፡ አብዛኛው

የዓለም ህዝብ መፃፍና ማንበብ ሲችል በማህበራዊ ሚድያም መልክቶችን በቀላሉ መለዋወጥ ችሏል።

ዛሬም ሚሊዮን በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ የጌታ ልጆች በዓለም ዙሪያ በኢትዮጵያም ጭምር ስላሉ የእግዚአብሄር ማዳን ስራ በልጆቹ ይቀጥላል። በዚህ ዘመን ቤተክርስትያን ልታካሂድ የሚገባት ብርቱ ጉዳይ ዓለምን ቤተክርስቲያንን ሳይቀር የከበባትን የሰይጣን ጨለማ በቅዱስ ቃሉና በብርቱ ጸሎት መጠራረግ ማስወገድ ነው። 'በመጨረሻው ቀን ከመንፈሴ አፈሳለሁ' (ሐዋ 2÷17)

## መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ምጽአት

'መንፈሱና ሙሽራይቱም ና ይላሉ' (ራእይ 22÷17)

የመፅሐፍ ቅዱሳችን የመጨረሻው መፅሐፍና የመጨረሻው ምዕራፍ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያሳስብ የምልጃ መሆኑ አስደናቂ ነው።

ጌታችን ከማረጉ በፊት የተከናወኑ ተግባሮችን በሚገልጹበት መፅሀፍ ቅዱሳችን ምዕራፎች ይህንኑ ዳግም ምጽአት የሚያተጉ ምክሮች የመንፈስ ቅዱስን የቃልኪዳን ተስፋ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሚያፈስሰውን ይተነትናሉ።

ጌታ ሆይ ቶሎ ና ማራናታ የሚለው ድምጽ በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ምሪት ክርስትያኖች የጌታን ዳግም ምጽአት በቅድስና በሀሴት እንዲጠብቁ ስለሚያሳስብ ለእኛ ለባለተስፋዎቹ አማኞች የጌታ ዳግም ምጽአት ምሥራች እንጂ መርዶ አይደለም፤ አያስደነግጠንም፤ ብርታት ይጨምርልናል እንጂ። 'የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ስትተባበቁ አንድ ጸጋ ስጦታ እንኳ አይጎድልባችሁም።' (1 ቆሮ 1÷7)

መንፈስ ቅዱስ በቅዱስ መጽሐፉ የተነገሩትን ቃላት በኃይል በሙሉ በመረዳት አማኞች እንዲያውቁትና በህይወት እንዲተረጉሙት ያበቃል።

የእግዚአብሄር ቃልን በሰሙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በልዩ ሀይል መረዳትን ሰጣቸው። የመሲሁን ክርስቶስ መምጣት ይጠባበቁ የነበሩት የመቅደሱ አገልጋዮች ስምኦንና ሀና ምስክሮች ናቸው።

'የየሩሳሌምን ቤዛ ለሚጠባበቁ' (ሉቃ 2÷38)

በዘመናችንም ቅዱስ ቃሉን በሰሙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ ከመፍሰስና ከመገለጥ የሚከላከል ነገር ከኃጢያት በስተቀር አንዳች የለም።

ዓለም በእውነት የመንፈስ ቅዱስን ስራዎች እንቅስቃሴዎች ብትሳለቅም ብትገፋውም ዛሬም መንፈስ ቅዱስ እንደተስፋ ቃሉ በሕዝቡ ላይ ይሰራል ያላመኑትን ልብ  በመንካት ለዘላለም ህይወት ያበቃል ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሀኑ ይመልሳል።

'መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።' (የሐዋርያት ሥራ 1÷8)

## ራሳችንን ለክርስቶስ ምጽአት እናንፃ

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ህይወቱን ለእኛ በከፈለበት ወቅት የገለፀው ትልቁን ከፍተኛውን የፍቅር ደረጃ ነው።

‹‹ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም››

(ዮሐ 15÷13) ይህንን ለአማኞች ለቤተክርስትያን የሰጠውን ፍቅር ኤፌሶን 5÷25 ላይ እናነባለን ይህንንም ፍቅር የገለፀው ክቡር ደሙን ለሰው ልጅ በማፍሰስ ነው (1ጴጥ 1÷18-19)

ጌታ ለአማኞች (ቤተክርስትያን) የከፈለውን ትልቅ ልዩ መስዋእትነት ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ ምንም ጥያቄና ጥርጥር የሌለበት ልዩ ፍቅር ነው።

'ኃጢያትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም ታላቁን አምላካችንንና የመድሀኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ እየጠበቅን ራሳችንንም በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁን ዘመን እንድንኖር ያስተምራል።' (ቲቶ 2÷13)

በየቀኑ በኖርን ቁጥር የጌታ ዳግም ምጽአትን እየቀረብን መሆናችን የታወቀ ነው። በዚያች የመጨረሻዋ ብሩህ ቀን ያዳነን ጌታችንን እናየዋለን።

‹‹ምን እንደምነሆን ገና አልተገለጠም ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን›› (1 ዮሐ 3÷2)

በዚህች ለኮንድ ይህንን መልክት በምታነቡበት ሰዓት የጌታን ዳግም ምጽአት በመጠበቅ እየኖራችሁ ወይንስ በልባችሁ ሌላ ኃጥያት እያስገባችሁ ለውድቀት ከጌታ ለመለየት እየፈጠናችሁ ነው?

ሀዋርያው ግን እንዲህ ያሳስበናል በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢያት አያደርግም ኃጢያትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውም። (1ዮሐ 3÷5) በብዙ መስዋእትነት ጌታ ያጎናፀፈንን ዘላለማዊ ስጦታ በቀላሉ በኃጢያት ከጌታ በመለየት እንዳናጣው በጥንቃቄ ጸጋውን እንጠብቅ

'የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኃላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለኃጢያት መሥዋት አይቀርልንምና። የሚያስፈራን ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችን ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ። የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሶስት ቢመሰክሩበት ያለ ርህራሄ ይሞታል። የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን ደም ያከፋፋ እንዴት የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኃል።' (ወደ እብ 10÷26-28)

**የጌታን ጥሪ ለማይቀበሉ ፍርድ አለ**

ከሁሉ በላይ በዚህ ወቅት የሚያሻን ወደ ቀደመው ፍቅር የሚመልስን ነ-ዛዜና ንስኃ መንፈሳዊ መታደስ ማግኘት ነው።

ከእግዚአብሔር በመለየታችን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ከመቼውም ጊዜና ታሪክ በበለጠ በዚህ ግዜ ያስፈልገናል።

ምድራችንና ህዝባችንን ለማዳን የዚህ ዓይነቱ የንስኃ ሂደትና መነቃቃት በጣም ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ መታደስና መነቃቃት የሚረዳውን ቅዱስ መንፈሱን ያፈስብን ዘንድ ቃል ገብቷል። (ዘካ 12÷10)

እያንዳንዱ በእየራሱ በዚህ መንፈስ ራሱን ቢያዘጋጅ እግዚአብሔር እኛን ተጠቅሞ ሚሊዮኖችን ያድናል። (ኢዩ 3÷14)

በእግዚአብሔር ፀጋ ተደግፈን ለዚህ ወሳኝ የጸሎትና መንፈሳዊ መነቃቃት ሂደት ልንተጋ ይገባል። ብዙዎችን ከወደቁበት አዘቅት በዚህ መንገድ ብቻ መታደግ ይቻላል።

‹‹የመዳን ቀን ዛሬ ነው›› (2ቆሮ 6÷2)

ከተወሰነ ጊዜ በኃላ በንስኃ ወደጌታ መመለስ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። ዛሬ ሁኔታዎች የበለጠ ሳይጨልሙ በጌታ ቃል መድረስ እንችላለን።

በትክክል ዓለማችን የተበላሸ ማህበረሰብ ቤተሰብና ሀገር ስላፈራች የክርስቲያኖች ለዚህ በፆምና በጸሎት በመትጋት ትልቅ እድል ነው። የምህረት በር ከተዘጋ በኃላ ማንም ቢጮህ ቢያነባ ሊከፍትለት አይችልም።

የመዳን የምህረት ቃል በተነገራቸው ጊዜ ለማይዘጋጁት እምቢ ብለው በክፉ ስራቸው ለቀጠሉ ድጋሚ እድል የለም። (ማቴ 25÷19) (ገላት 6÷7) (ሆሴዕ 8÷7)

እግዚአብሔር አይዘበትበትም ክርስቶስን ያለመቀበልና የእግዚአብሔርን ምህረት የመንፈስ ቅዱስን ፍቅር እምቢ ለሚል ሥርየት የሌለው አካሄድ ስለሆነ መጨረሻው ገሀነም ነው። (ማቴ 25÷46)

እግዚአብሔር መጨረሻ ፍርዱን እስኪልክ ድረስ ከመጠበቅ ዛሬ ምህረቱ ሲቀርብልን ከኃጢያት ተመልሰን ይቅርታውን ተቀብለን እንድን ዘንድ ይገባል።

የእግዚአብሄር ፍርድ ከቤቱ እንደሚጀምር ቃሉ ስለሚያስጠነቅቀን በክርስቶስ በማመን ደህንነት ያገኘን ሁሉ ተጠብቀን መዳናችንን በእግዚአብሔር ፍርሀት እንንፈፅም።

(ዘፍ 32÷26፣ሕዝ 9÷4፣1 ጴጥ 4÷17)

ወንዶችና ሴቶች የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ ለመንፈሳዊ ተሀድሶ ለመንፈሳዊ መነቃቃት እንነሳ ራሳችንም ሌሎችም ከወደቁበት ኃጢያት በጊዜ በቃሉና በጸሎት በመንፈስ ቅዱስ ድጋፍ እንነሳ እንትጋ እናትጋ እንፈወስ። (ዳንኤል 9÷1-23 ማቴ 5÷13)

**ሙሽራይቱ ተዘጋጅታለችን?**

በሠርግ ላይ ለመታደም ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችና ምክንያቶች ሲኖሩ የእንግዶች አይነት፤መቀመጫ፤ሻማ፤ዝማሬና የመሳሰሉት ሲጠቀሱ ከሁሉ በላይ ወሳኙ ግን የሙሽራይቱ መዘጋጀት ነው።

ሙሽራይቱ በበቂ ሁኔታ እስካልተዘጋጀች ድረስ ሙሽራው ወደ ሙሽሪት ቤት ገብቶ ሊወስዳት አይችልም። ሙሽራይቱ ተዘጋጅታ እንዳትገኝ መሰናክል የሆኑ ብዙ ነገሮች እናውቃለን።

በዚሁ መልክ ሙሽራይቱ ቤተክርስቲያን የአማኞች ህብረት ለሙሽራው ለክርስቶስ ካልተዘጋጀች ወደ ሙሽራው መቀላቀል መነጠቅ መወሰድ አይሆንላትም።

የሙሽራይቱ የቤተክርስትያን ባማረ ሁኔታ መዘጋጀት ያለነቀፋ ያለኃጢያት በቅድስና መጠባበቅን ራዕይ 19÷7 ያሳያል።

'የበጉ ሰርግ ስለደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሴትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ። ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጎናፀፍ ተሰጥቷታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።'

ጌታችን ሙሽራ ሆኖ ሙሽራይቱ ቤተክርስቲያንን እንደሚወስድ የተፃፈው በአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም ጭምር ነው። (ትንቢተ ኢሳያስ 62÷5)

ቤተክርስቲያን የቀደመ ውበቷን አጥታ ስትጎሳቆል በኃጢያት ስትቆሽ ጌታ በቅዱስ ቃሉና በመንፈሱ ያነቃቃታል። (ኤር 2÷2÷32)

እግዚአብሔር ፍቅሩን ለቤተክርስቲያን ለአማኝ ልጆቹ የሚገልፀው ፍቅር ከባልና ከሚስት መዋደድ የበለጠ ምሳሌያዊ ዘይቤ የለም። በመፅሐፍ ቅዱስ በስፋት የሚገለፀው ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ልዩ መለኮታዊ ፍቅር ነው።

ዛሬ ቤተክርስቲያን ሙሽራይቱ የአማኞች ህብረት የቅዱሳን ጉባኤ ለሙሽራው ለክርስቶስ ልትዘጋጅ የሚገባው ቀን ነው። ወደጌታ ዳግም ምጽአት

በቀረብን ቁጥር ቤተክርስቲያን የሙሽራይቱ አማኞች ህብረት ይበልጥ መዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

ሙሽራይቱ እንዴት መዘጋጀት እንዳለባት ለማስተማር መፅሐፍ ላይበቃ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህንን ታላቅ ዝግጅት በቀላሉ ለመፈፀምና ለዳግም ምጽአቱ ለመዘጋጀት ቅዱስ መፅሀፍ እንደሚያስተምረው ሙሽራይቱ የሙሽራው ብቻ መሆኗን አምኖ ተጠብቆ መቆየትና ከነቀፋ ከሀጥያት ዘወትር በበጉ ደም ተቀድሶ መቆየት ነው፡፡ (2 ጴጥ 3÷14፣ራዕ 21÷2)

### ክርስቶስ ለቤተክርስትያን ያለው ፍቅር

'ክርስቶስ ዳግም ቤተክርስትያንን እንደወደዳት' (ኤፌ 5÷26)

ክርስቶስ ህይወቱን በሙሉ ለቅድስት ቤተክርስትያን ለአማኞች ህብረት ሰጥቷል፡፡ የክርስቶስ ህይወትና ገሆ ሕይወቱን በሙሉ ለቤ/ክ (ለአማኞች ህብረት) መትጋት መድከምና በመጨረሻ መታረድ ነው፡፡

ክርስቶስ ገና ሲወለድ የምስራች ዛሬ በቤተልሄም በዳዊት ከተማ የዓለም መድሀኒት ተወለደ ከሚለው ጀምሮ በመስቀል ላይ ህይወቱን ለሰው ዘር በመስጠት 'ተፈፀመ' እስካለበት ድረስ ለሰዎች ደህንነት የኖረ ጌታ ነው፡፡

በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ወቅት በሚስማር የተወጉት እጆችና እግሮች በጩኸኝ ገገርዎች በራሱ ላይ የተጻፈበት የእሾህ አክሊል የተነሳ የፈሰሰው ደም ነው፡፡ ጌታ በመስቀል ላይ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ በአረማይክ ቋንቋ ‹‹ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ›› ያለው ለአባቱ በስጋው የደረሰበትን ለሰው ዘር የከፈለውን መከራ ለማሳየት ድምጹን ያሰማበት ጊዜ ነው፡፡

ሴቶቹ ብቻ ቀርተው በመስቀሉ ዙሪያ ሲያነቡለት የአርማትያሱ ዮሴፍ የመቀበሪያ ስፍራውን ሲያዘጋጅለት የምንረዳው ይህንን ለሰው ዘር ያለውን ልዩ መለከታዊ ፍቅር ነው፡፡

ክርስቶስ ፍቅሩን ለመግለጽ ለእኛ በኃጢያት በተጸነስነው በኃጢያት በኖርነው ለሰው ልጆች ምትክ የኃጢያታችንን የበደላችንን ቅጣት በመስቀል ላይ ከፍሎ ሞተልን፡፡
ክርስቶስ ህይወቱን በመክፈል ከፍተኛውን የፍቅር ደረጃ ለሰው ዘር ሁሉ አሳየ፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ተቀበረ፤ ወደ ኃጢያተኛ (እምቢተኛ) ሰይጣን መጣያ ስፍራ ወደተዘጋጀው ወደ ሲኦል ወረደ፡፡ ይህ ሁሉ ስቃዩና መከራው ተከፈለልን፡፡ እኛ የሰው ልጆች በተለይ ይህ ሚስጥር የተገለፀልን አማኞች በደስታ ልንመሰክር ይገባል፡፡

ዛሬ ክርስቶስ ሞትን በትንሳኤ አሸንፎ ህያው ሆኖ በመንፈስ በመካከላችን እስከ ዓለም ፍጻሜ እንደሚኖር በሰጠን ተስፋ ይኖራል፡፡

ለዘላለም የሚኖረው ሊቀካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ዘወትር የሚማልድ የሚማለድ ጌታ ሰውና አምላክ የሆነ ነው፡፡ (1 ጢሞ 2÷5 ዮሐ ወንጌል 14÷5 ሮሜ 8÷27)

ይህ ሰውም አምላክም የሆነው ክርስቶስ ጋር ያለኝ ግንኙነት ያማረ ሆኖ እስከመጨረሻው ልፀና እመኛለሁ እፀልያለው እመሰክራለሁ፡፡ እናንተም በክርስቶስ ያመናችሁ ይህ ሙሉ መብትና ኃላፊነታችሁ ነውና ትጉበት፡፡

### አምስቱ የጽድቅ አክሊሎች

ከጌታ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት በኃላ ለአማኞች የሚሰጡ አምስት የጽድቅ አክሊሎች ተዘርዝረዋል

'እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመዎዝ ይቀበላል።' (1 ቆሮ 3÷8)

**አንድ፡- የደስታ አክሊል**

የደስታ አክሊል ነፍሳትን ለክርስቶስ መንግስት ለሚያቀርቡት ይሰጣል።

‹‹ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁንም?›› (1 ተሰ 2÷19)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ በሄደበት ወቅት ሦሥት ሰንበት ወንጌል ሰብኳል በአገልግሎቱ ማብቂያ ላይ ግን ከዚያ ተገፍቶ ተባርሯል ብዙ ሰዎች ግን በአገልግሎቱ በክርስቶስ በማመን ድነዋል።

**ሁለት፡- የጽድቅ አክሊል**

‹‹የምሄድበትም ጊዜ ደርሷል መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቂአለሁ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም›› (2 ጢሞ 4÷1) የጽድቅ አክሊል ጌታን ለሚጠባበቁ ይሰጣል።

**ሶስት፡- የክብር አክሊል**

'የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።'(1 ጴጥ 5÷4)

የክብር አክሊል የእግዚአብሔርን መንጋ በሚገባ ለሚጠብቁት ፓስተሮችና መጋቢዎች የሚበረከት ነው። ከዚህም ጋር ሌላም ሽልማት ጌታ በክብር ሲገለጥ አብሮ መክበር ነው።

**አራት፡- የማይጠፋው አክሊል**

'የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል። እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው። እኛ ግን የማይጠፋውን።' (1ቆሮ 9÷25)

ሐዋርያው ጳውሎስ የሚቀበለው ሽልማት የሚጠፋውን ከምድር የሆነውን ሳይሆን የዘላለሙን የሰማያዊውን አክሊል እንደሚቀበል ደጋግሞ ተናግሯል።

**አምስት፡- የህይወት አክሊል**

የዚህ አይነቱ ሽልማት ሁለት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን በሲምረን ላለች ቤተክርስትያን ጸጸት ለተቀበለች እንደሚገባ ተጽፏል ‹‹ እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የህይወትንም አክሊል አሰጥሃለሁ›› (ራእይ 2÷10)

የዚህ አይነቱ አማኝ በፈተና በመከራ የሚፀናውን ይመለከታል (ያዕቆ 1÷12) ኃጢያት ያስከተለ ፈተና ስለሆነ ፈተና ማለፍ ይገባል።

**የክርስትና መለያ ክርስቶስ ነው**

‹‹ጌታ ቅርብ ነው›› (ፊል 4÷5)

ጌታ ቅርብ ነው የሚለው አባባል የሐዋርያቱ የተለመደ ንግግር ነበር። የሐዋርያቱ የጌታን ቅርብነት በጊዜ በሥፍራና በሁኔታዎች ሁሉ ይጠቅሱት ነበር።

አዎን ጌታ ቅርብ ነው። ክርስቶስ አስከዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ ባለው የህይወት ተስፋ ቃል መሰረት ከሚያምኑ ልጆቹ ጋር በጣም ቅርብ ነው። (ማቴ 28÷20)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአማኝ ልጆቹ ያለው ቅርብነት በሚከተሉት ሥሥት ሁኔታዎች ይገለፃል፡-

1. ጌታ ቅርብ ነው ሳታቋርጡ ጸልዩ

‹‹ ባለቤቱ መች እንደሚመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ›› (ማርቆስ 13÷36)

ጌታችን በትክክል ዳግም ስለሚመጣ አማኞች በጸሎት ተጠብቀን ልንገኝ ያስፈልጋል። ጌታ ዳግም የሚመጣበትን ሰዓት ማንም ስለማያውቅ በኃጢያት ጎድለን እንዳንገኝ ራሳችንን በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለማቆየት ዘወትር እንጸልይ።

ጸሎታችን በሀቅ በሙሉ ኃይል በቅንነት በጌታ በብርሃኑ እንድንመላለስ ይሁን።

በጌታ ስራ የተሳካላቸው ሁሉ ልዩ የጸሎት ህይወት የነበራቸው ናቸው።

ብዙዎች ልዩ ልዩ ስጦታዎች ያላቸው አገልጋዮች ከጸሎት ህይወት መጉደል የተነሳ ሲወድቁ ወደኃላ ሲመለሱ ይታያል።

የጌታን ፊት በጸሎት ሳንጠይቅ ቃሉን ሳናጠና ለችግራችን ወደሰዎች መሄድና መፍትሄ መጠየቅ ያለማስተዋል ነው። ጌታ ቅርብ ነው ቅርብነቱ ከእርሱ ጋር በመንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ፈቃድ በብርቱ ጸሎት በመጠየቅ በማወቅ ይረጋገጣል።

2. ጌታ ቅርብ ነው

‹‹ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሱ›› (ያዕቆ 5÷7)

ጌታችን ቅርብ በመሆኑ በክርስትና አገልግሎታችን እየተጋን የወንጌሉን ቃል እንዝራ እንመስክር በሚያጋጥሙን ፈተናዎችና መከራዎች ሳንበገር የጌታ መንፈስ ቅዱስን ብርታት እየጠየቅን እንፅና።

3. ጌታ በንፅህና እንጠብቅ

በጣም ጠንካራና መልካሙ የእግዚአብሔር ቃል በንፅህና ያለነቀፋ መገኘትን መከተል ነው። ‹‹በእርሱም (በጌታ) ይህን ተስፋ የሚያደርጉ ሁሉ እርሱ ንፁህ እንደሆነ እራሱን ያነፃል›› (1ዮሐ 3÷3 )

ሐዋርያው ጳውሎስ ዓለማዊ ምኞትን ሥራን ክዳን በተቀደሰ ህይወት የጌታን የተባረከ ተስፋ እንድንጠብቅ ይመክራል (ቲቶ 2÷12)

ሐዋርያው ጴጥሮስም ተመሳሳይ ቃል ይናገራል (2ኛ ጴጥ 3÷11)

አማኞች ጌታ እንዲጠቀምብን መሻቱ ካለን ከዓለም በመለየት ሁል ጊዜ በክርስቶስ እንኑር።

**ወሳኝ ጥያቄ፡- ለምጽአቱ ተዘጋጅታችኃል?**

ጌታ ፈጥኖ ይመጣል ሙሽራው ክርስቶስ ሙሽራይቱ ቤተክርስትያን (የቅዱሳን አማኞች) ጉባኤን ሊወስዳት ይመጣል። የክርስቶስ ሙሽራ በምን መልክ ተውባ ጌታን እንደምትጠባበቅ በመዝሙረ ዳዊት 45÷11 ተዘርዝሯል።

ክርስቶስ ጌታን የምናመልከው በጸዳል ግርማ ተሞልቶ ነው። ይህ የእግዚአብሔር የጌታ ግርማ ሞገስ ለሙሽራይቱ ለቤተክርስትያንም የተትረፈረፈ ክብር ነው (1 ዜና 16÷29)

የቤተክርስትያን ውበት ፊት መጨማደድ የሌለበት ሁሌም በክርስቶስ የደሙ ኃይል ጌታ መንፈስ ቅዱስ ክብሩን የሚያንፀባርቅባት ነች። (ኤፌ 5÷27) ስለዚህም ቅድስት ቤተክርስትያን ራሷን ያዘጋጀች ነች። (ራእይ 19÷7)

የእኛ ሀላፊነት ግዴታ መዘጋጀት ነው

የቤተክርስትያን የበኩር ልጆች ደናግሎች ማለትም ለጌታ ስራ የተለዩ ናቸው።
ሀዋርያው የእምነት ልጆቹን በዚህ መልክ ለጌታ የተለዩ መሆናቸውን ፅፎልናል።

'እንደ ንፅህት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁ።' (2 ቆሮ 11÷2)

ክርስትያኖች ሆይ ውስጣችሁ ክብር ገብቷልን? የለበሳችሁት መጎናፀፊያ ያለ አንዳች እድፍ ነውን? ጌታ የቆሸሸ መጎናፀፊያችን እንዲወገድ እንድንቀየር ይፈልጋል። (ይሁዳ 23)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁላችንም በቅድስና በንፅህና እንድንኖር ከነውርና ከእድፈት ተጠብቀን እንድንገኝ ይመክራል (ሉቃ 21÷34)

ጌታ ለተከታዮቹ ሲያስተምረን ሁልጊዜ ወደፊት በመራመድ አዲስ ልምምድ እንድንቀበል እንጂ ያለፈውን በረከት በመቁጠር የምንደነዝዝ እንድንሆን አይደለም። (1 ሉቃ 21÷34)

የእምነታችን ጀማሪና ፍፃሜ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ በቅዱስ ቃሉ ያሳሰበን እንድንተጋና እንድናስተውል ነው። በዚህም የሰይጣን የዓለምና የስጋ ተግዳሮቶችን በመመከት በቅድስና ተጨማሪ በረከት እናገኛለን። (ማር 13÷37) ‹‹ትጉ››

ለጌታ መትጋት ከጌታ ጋር በቃሉ ጥናት በጸሎት በመቆየት ይገኛል። ‹‹ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን›› (ሉቃ 13÷24)

በጌታ ዳግም ምፅአት አንዷ ስትወሰድ ሌላዋ የምትቀረው ለትምህርት ይሁነን። (ሉቃ 21÷35)

የጌታ ዘላለማዊ ጸጋን በልጁ በክርስቶስ ስላገኘን ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዘወትር የተዘጋጀን የተጠበቅን እንሁን።

## ለቅድስና የሚያበቃ ትምህርት

የጌታ ዳግም ምጽአት የዓለም ፍጻሜ ትርክት የብርቱ ጸሎትና በጌታ ፊት መቆየት የቅድስና ህይወት ያቀፃጃል።

የጌታ ዳግም ምጽአት ማንም ስለማያውቅ በቅዱስ መጽሐፉ የተሰጡ ምልክቶችን በማጤን ልንዘጋጅ ልንበረታታ ይገባል።

የጌታ ዳግም ምጽአቱ በማንም የማይታወቅ ከሚታዩት የማስጠንቀቂያ ምልክቶች በመነሳት ከአገልግሎት አጋሮቻችን ጋር ደግሞ ምጽአቱን በሚገባ እንጠብቅ።

**የዳግም ምጽአቱን መጠበቂያ ዘዴዎች**

1. **ራሳችንን ዝግጁ የማድረግ ሂደት**(1 ተሰሎ 1÷9-10)
2. **ተስፋ፡-** የምንጠብቀው ተስፋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ክፉ ሰይጣን ግን አዘናጊ ነው።(1 ቆሮ 3÷13)
3. **ያለነቀፌታ መገኘት፡-** የጌታን ዳግም ምጽአት ከልባችን በመንፈስና በቃሉ ተቀድሰን በንፅህና መገኘት
4. **ማፅናናት**
   ‹‹ እርስ በእርሳችሁ በዚህ ቃል ተፅናኑ›› (1ኛ ተሰሎ 3÷18)ትንሳኤ ስለሚኖር በህይወት ያሉትም ስለሚነጠቁ በህይወት ያለን እርስ በእርስ በመፅናናት ጌታን እንጠብቃለን።
5. **መንፃትና መቀደስ፡-** 'ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽሞ ይጠበቁ' (ተሰሎ 5÷23) አማኞች ነፍስ አካልና መንፈስ በክርስቶስ

የተዋጀ በመንፈስ ቅዱስ ከክፉ የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡

6. ***መፅናት መረጋጋት***
‹‹በቃል ወይም ከእኛ እንደ ሚመጣ በመልዕክት የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ከአእምሯችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን›› (2 ተሰ 2÷2)

7. ***ትዕግስት***
‹‹ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትእግስትም ልባችንን ያቅናው፡፡ (2ተሰሎ 3÷5)

እነዚህ መሰረታዊ የዳግም ምጽአቱ የመጠበቂያ ማሳሰቢያዎችን ሁሉም ክርስትያን ሰምቶ መጠበቅና በቃሉ መፅናት ይኖርበታል፡፡

በእርግጥም ጌታ ይመጣል አዋቹ ግን ስለሚያስት እንጠንቀቅ እንረጋጋ፡፡

**የየእለቱ ኑሮአችን ተስፋችንን ይከተል**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አንተን በተስፋ እንጠብቃለን በዙሪያችንም ያለው ዓለም በስጋችን ሊያደክመን ሊያስተን በብዙ ይታገለናልና ወደቤትህ እስክንደርስ ድረስ ናፍቆታችን በዝቷል - ጌታ ሆይ ቶሎ ና!

ይህ ቃል በመንፈሳዊ መነቃቃት የዚህ ዓለም ነውርና እርኩሰት የማይበግረው የክርስታያኖች ጩኸት የተሰማው የመነቃቃት አገልጋይ የተዘር ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስን ለመቀበል ወይም ወደ እቅፉ ወደ ዘላለሙ ቤታችን ለመግባት ክርስትያኖች የሚከተሉትን እንፈፅም፤

**ኃጢያታችንን እንናዘዝ**

በምንም አይነት መልኩ ጌታ መንፈስ ቅዱስ የሚያሳስበን ኃጢያት ያለ ንስኃ በእኛ ዘንድ መቆየት የለበትም የሚሰማንን የሚታወቀንን በደል ስህተት ኃጢአትና ክፋታችንን ለጌታና ለበደልነው ሰው ከልብ በመንገር እንናዘዝ፡፡

የመናኝ ጉዞ በኃጢያት ሸክም በመንገዳገድ ሳይሆን የኃጢያት ሸክሙን በጌታ እግር ሥር በኑዛዜ በመጣል ነፃ ሆኖ ያለሸክም ወደ ቅድስት ኢየሩሳሌም ጽዮን ቤታችን መጓዝ ነው፡፡

ኃጢያት መቸም ቢሆን ከጌታ የሚለየን ክፉ ነገር ነውና እንፀየፈው በፈተና ከወደቅንም ፈጥነን ለጌታ እንናዘዝ፡፡ (1 ዜና 7÷14)

በየቀኑ የጌታን ቃል ተመገቡ ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ እንጂ ብሎ ጌታ ራሱ ያስተማረን የእግዚአብሔርን ቃል አስፈላጊነት በሚገባ ስለሚያስረዳን ቃሉን እንመገብ፡፡(ማቴ 4÷4)

ለሰውነታችን ምግብ ስናጣ ስጋችን ሰውነታችን እንደሚከሳ ሁሉ ለነፍሳችን ቃል ካልመገብነው ነፍሳችን ትኳሳለች፡፡

**ዘወትር ዘወትር ፀልዩ**

ቃሉን በማንበልበል ብቻ ሳይሆን በመንፈስ በመረዳት በቃሉ በመመለስ ለጉዳዮቻችን ለሰዎች መዳን ለነፍስና ለስጋ ፈውስ ለመሪዎችና ለሀገር በብርቱ መፀለይ የክርስትያኖች ሁሉ ኃላፊነትና ጥቅም ነው፡፡ ለጸሎታችን እንግፋበት፡፡ (1 ዮሐ 5÷15)

ለጸሎታችን ደጉ አባታችን ጌታ እንደሚመልስ በሙሉ በመተማመን ቃሉን መሰረት በማድረግ እንፀልይ (ማቴ 7÷11)

የዘወትር ጸሎታችን ናፍቆታችን የፍቅር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ይሁንልን አሜን!

## ኢየሱስ ባልታሰበ ቀን በክብር ይመለሳል

በእለቱ ኑሮአችን ልዩ ልዩ ጉዳዮች ስናከናውን እንውላለን ጌታንም አልፎ አልፎ እናስባለን ወይም ደግሞ እንረሳለን ሆኖም ግን ጌታ እንደተስፋ ቃሉ ማንም በማያውቀው ጊዜና ሰዓት በክብር በኃይል በግልፅ ይመለሳል። (ሉቃስ 17÷34)

ቄስ ዶክተር ማርቲን ሉተር ጌታ ሲመጣ ምን ታደርግ ይሆን ለሚለው ጥያቄ የመለሰው ተገቢና ሁላችንም ልንመልሰው ይገባል። 'ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል ብሎ ቁጭ ብሎ ወይም እጆቹን ዘርግቼ አልጠብቀውም ነገር ግን የተለመደ የየእለት ሥራዬን ማረስ ቢሆን መስበክ ቢሆን መናገር ቢሆን ማስተዳደር ቢሆን ማጽዳት ቢሆን በተፈለገው ጤናማ ስራ ላይ ተሰማርቼ ጌታ ሲገለጥ አገኘዋለሁ።'

በማርቲን ሉተር መልእክት ህይወቱ የተለወጠው የሜተዲስት ቤተክርስትያን መስራች ጆን ዌስሊም ስለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የአማኞች መልክ ራእዩን ሲናገር ከእርሱ ከቀደሙት ባነሰ ብርሃን ከእነሱ ኂላ ሆኖ ማየቱን ሲናገር የእውነተኛ ክርስትያን የዳግም ምጽአቱንና አዲሲቱን እየሩሳሌም የጽዮንን ተስፋ ያሳያል። ጌታችንና መድኃኒታችን ወደዚህ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ በመጣበት ወቅት በመላእክት ልዩ ብርሀን እንደታጀበ በክብር ዳግመኛ በሚመለስበትም ወቅት ከፍተኛ ብርሀንና ክብር በሰማይ ላይ ይገለፃል። (ሉቃ 2÷9፤ማቴ 24÷30)

ዛሬ በመደበኛው የስራ ወይም የትምህርት የሽርሽር ወይም የሰው ጥየቃ ወይም የልዩ ልዩ ጉዳዮች መፈፀሚያ ቀናችን ላይ የጌታን ዳግም ምጽአት እንዴት እያሰብን ይሆን? በትክክል እንደተጻፈው ለሰው አንድ ጊዜ መሞትና ለፍርድ ድጋሚ መነሳት ስለሚኖር በፍርድ ወደገሀነም ከመጣል በምህረቱ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ዛሬ በዚህች ሰዓት በእምነት ጌታን እንቀበለው። (ዮሐ 1÷12፤ ዕብ 9÷27)

ጌታ በየትኛው ቀን ሰዓት ደቂቃ ወይም ሰከንድ እንደሚመጣ ማንም ስለማያውቅ ሁላችንም በቃሉ በመኖር በንስኃ በጸሎትም በመትጋት እንጠብቀው። (ማቴ 24÷44)

ይህን የሚያሳስበንን የጌታን ቃል በክብር እንጠብቀው። (2ጴጥ 1÷19)

## ልዩ ጸሎት ለኢትዮጵያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ቀድመው ከተጠቀሱት ሕዝቦችና መንግስታት የመጀመሪያዋ በመሆን ኩሽ ኢትዮጵያ የምስራቅ ሰዎች ከሚባሉት የተመደበች መሆኗ የሚታወቅ ነው።

በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከአርባ ጊዜያት በላይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ተወስታለች የበረከት ተስፋዎቿ የቁጣና የመርገም ማስጠንቀቂያዎቿም የተዘረዘሩ ናቸው ሁሉንም የጌታ ቃል በሚዛን በመጠበቅ በብርቱ ፆም ጸሎት መትጋት ይኖርብናል።

በቅርቡ በሀገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ልዩነት የተነሳ የደረሰብን መገዳደል መታረድ በተለይ በሰላም ሥፍራ የወንጌል ሥራ ብቻ ሊሰሩ በእጃቸው አንዳች ክፋት ያልተገኘ ፓስተር ኢሳያስና ወንጌላዊ አሰፋ በወለቴ፤ሰበታ፤በባሌ፤የተዋህዶ ቀሳውስወትና የሌሎቹም ክርስትያኖች መታረድ እጅግ የሚዘገንን የሀገራችን አስከፊ ገጽታ ሆኗል።

እኛ ውጊያችን ስጋዊ አይደለም። በጦር መሳሪያ የማንዋጋ ሁሉን ድል ማድረግ በሚችል በክርስቶስ

መንፈሳዊ ጦር የምንዋጋ አርበኞች ነን፡፡(ኤፌ. 6÷12)

ሆኖም ግን በጌታ ቃል በታዘዝነው መሰረት ለሀገር መሪዎች እንድንፀልይ ሰላምን የሚያስጠብቅ ልንደግፍ ወንጀለኞችን በፍፁም በአዳራሾቻችን እንዳናስተናግድ የሰው ዘር ሁሉ ሰላምና ፍቅር አስጠባቂ ነን፡፡ (ሮሜ 13፤1 ጢሞ 2÷2)

በክርስቲያኖች ጸሎትና ትጋት ባርነትና የቀኝ አገዛዝ ግፍ በዓለም ላይ እንዲወገድ ክርስትያኖች ለፍትህ ለመቆም ቀዳሚ መሆን ይገባናልና በዚህ በጎ ስራ እንትጋ፡፡

**ዓለም አቀፍ የጸሎት ርእስና ምስጋናዎች**

**ከፖላንድ**

ብዙዎች ለዚህ መንፈሳዊ መነቃቃት በመጸለይ ላይ ናቸው፡፡ ይህንን ጠቃሚ ጋዜጣ ስለምትልኩልኝ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

**ከዛሚቢያ**

የምጽአት የምስራች በጌታ የተቀባ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆኔ ጌታን አመሰግናለሁ ህይወቴን በልዩ ሁኔታ በመንካት የነፍስ ምግብ ነው፡፡

**ከእንግሊዝ**

ድንቅ ስለሆነው የስነጽሁፍ አገልግሎታችሁአመሰግናለሁ፡፡ ጋዜጣችሁ ህይወቴን በጣም ባርኳል፡፡

**ከአውስትራሊያ**

ለዓመታት ህይወቴን በቃሉ እንድፈትሽ ለረዳኝ ጋዜጣችሁ ልባዊ አድናቆቴን መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ እያንዳንዱ ርእስ ህይወት የሚቀይር ነው፡፡

**ከኢንድያና አሜሪካ**

የምጽአቱ የምስራች ልቤን በብርታት የሚሞላ ጋዜጣ ነው፡፡ በክርስቶስ ጠለቅ ያለ መንፈሳዊ ህይወት አለማምዶኛል፡፡

**ከደቡብ አፍሪካ**

የምጽአቱ የምስራች ጋዜጣን ስለምትልኩልኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በእምነት ጉዞዬ እንድጠነክር ያደረገኝ በጋዜጣው ላይ የሚሰፍሩት ድንቅ መልክቶች ናቸው፡፡

**ብርቱ የጸሎት ርእሶች**

በመላው ዓለም ክርስትያኖች ላይ የሚደርሰው ስደትና ግድያ ይቆም ዘንድ እንጸልይ በተለይ በህንድ በክርስትያኖች ላይ የሚካሄደውን ጥቃት ጌታ እንዲመክትላቸው አማኞችም እንዲጸኑ እንፀልይ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም እየተባባሰ የሄደው የዘረኝነት ጥቃትና የሰዎች ማፈናቀል ይቆም ዘንድ በያለንበት በብርቱ ጾምና ጸሎት ጌታን እንጠይቅ በክርስትና ስም እየተጠሩ በክፉ ዘረኝነት የተያዙትን ጌታ እንዲፈውስ እንጸልይ፡፡

**ማሳሰቢያ ለአንባቢዎች**

የምጽአቱ የምስራች በአንባቢያን መዋጮ በዓለም ዙርያ የሚሰራጭ የወንጌል መነቃቃት ጋዜጣ ነው፡፡

በአሜሪካ ያሉት አሳታሚዎች በመጠነኛ ኑሮ የሚኖሩ ስለሆነ በሀገራችን ያላችሁ ነፃ ተጠቃሚዎች ለአገልግሎቱ ጸሎት ድጋፍ የገንዘብ እርዳታችሁን እንጠይቃለን፡፡

## ልዩ ልዩ ክርስትያናዊ ዜናዎች

### የዩናይትድ ሜተድስት ቤተክርስትያን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለመኖር ወሰነ

የቅድስና እንቅስቃሴ በአውሮፓ በማስጀመር ወደአሜሪካ ያስፋፋና የመንፈሳዊ መነቃቃት ጌታ የጀመረባቸው የነ ጆን ዌስሌ ማህበር የሜተዲስት ቤተክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚፃረር የወንድ ለወንድ የሴት ለሴት ጋብቻ እንደማይቀበል ተስማማ።

ይህ ውሳኔ በብዙ የአሜሪካ ዜጎች ዘንድ የማይደገፍ ቢሆንም ትክክለኛው ጋብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለፀው ብቻ መሆኑን መሪዎቹ ተናግረዋል።

ጌታን በሜተደስት ቤተክርስትያን ስለ ላከው የእርምት መንፈስ እናከብረው እነሱንም እናመሰግናለን።

### በየሀገሩ ለሚካሄዱ ምርጫዎች እንጸልይ

በግሪክ በኢትዮጵያ በሌሎችም ሀገሮች የመንግስት ምርጫ ሊካሄድ በዝግጅት ላይ ነው። ሕዝቡ ሰላም የሚሰጡ እንዲመረጡ በዘር በሀይማኖት ፓለቲካ የማይከፋፍሉትን እልቂት ጥላቻ የሚቀሰቅሱ እንዳይመርጥ ሁላችንም እንፀልይ። መምረጥ የምንችል በእውነት ለሕዝባቸው በቅን የሚተጉትን የሰላም ሰዎች የአንድነት ሰዎች የምህረት ሰዎች የፍቅር ሰዎች እንምረጥ። ከጥላቻ ከዘረኝነት እንራቅ።

### የቤተክርስትያን ጥቃት እንዲቆም እንጸልይ

በኢትዮጵያ በህንድ፤በቻይና፤በሰሜን ኮርያ፤በቱርክ የሀይማኖት አክራሪዎች በክርስቲያኖች ላይ የሚያካሂዱት አሰቃቂ ግድያና ማፈናቀል እንዲቆም አንጸልይ።

### ለቬንዙዌላ ቀውስ እንፀልይ

በነዳጅ ሀብት ከላቲን አሜሪካ ሀገሮች ቀዳሚ በሆነችው ቬንዙዌላ የሚደረገው ሁከትን ጌታ እንዲገታ እንፀልይ። የቬንዙዌላ ሕዝብ ከፖለቲከኞች ሴራ በመራቅ በፍቅር ተባብሮ ይኖር ዘንድ መፀለይ ይገባናል።

### ለእስራኤል መፀለይ

የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ ሆና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለምትጠቀሰው እስራኤል እንፀልይ።

ፍልስጤሞች ሆኑ አይሁድ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች የክርስቶስ ቤተሰቦች ስለሆኑ በጸሎት እንትጋላቸው።

### የመዳን ምክሮች

1. ኃጢያተኛ መሆናችንን ቅዱስ መጽሐፍ በማንበብ መረዳት እንናዘዝ (ሮሜ 3÷23 6÷23)
2. ከኃጢያት ክፉ መንገዳችን ወደ ጌታ እንመለስ (ኢሳ 55÷71)
3. ክርስቶስ ለኃጢያታችን ተሰቃይቶ እንደሞተና እንደተነሳ በማመን እንከተለው። (ሮሜ 10÷9 ሐዋ 2÷38)

**የምጽአቱ የምስራች የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት ፣ አሣታሚ ሪቺ ካርማይክል የተባበሩት አሜሪካ ፣ተርጓሚ አስተባባሪ አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቴ መካሻ፣ የኢትዮጵያ ተጠሪ አልማዝ አሳየ**

**የፖ.ሣ.ቁ 8986 ስልክ 0912120402**

**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**